# ባሻ አሸብር ባሜሪካ

ባሻ አሸብር በአሜሪካ
የዛሬ አሥር ዓመት በታላቅ ሹመት
አሜሪካ ልኮኝ ነበረ መንግስት።

ዋሽንግተን ገብቼም ዋልሁ አደርሁኝና
ሽር ሽር ሳለ ባንድ አውራ ጎዳና
አላፊ አግዳሚውን ጥቁሩን ነጩን
ሳይ ስመለከተው በኢትዮጵያዊ ዓይን
የውሃ ጥም ደርሶ ስላረገኝ ቅጥል
ከመንገድ ዳር ካለች ካንድ ትንሽ ውቴል
ጎራ አልኩና ገና ከወምበር ላርፍ ስል
ተንደርድሮ መጣ የውቴሉ ጌታ
አማረው ቋመጠ ከጀለው ሊማታ።

«አብዱል ሰክሯል እንዴ ? ምንድን መሆኑ ነው ?
በል ንካኝ በዱላ ግንባርህን ላቡነው !»
ብዬ ስነጋገር ሰምቶ ባማርኛ
አሳላፊው ሆነ አስታራቂ ዳኛ
ለጥ ብሎ እጅ ነሣና እንዳገራችን ሕግ
አክብሮ ጠየቀኝ ምን እንደምፈልግ።

እኔም ጎራ ያልሁት የሚጠጣ ነገር
ለመሻት መሆኑን ነግሬ - ከወንበር።
«ይቅርታዎን ጌታ አዝናለሁ በጣሙ
ምናምኒት የለም በከንቱ አይድከሙ»
አለና እጅ ነሳኝ ሳቁን እየቻለ።
«ውኃም የለ ?» ብለው በሳቅ ገነፈለ።

ቤቱን የሞላው ሰው ሁሉም አጨብጭቦ
«ብራቮ ! ተባለ ብራቮ ! ብራቮ !»

በጣም ተገርሜ ደንቆኝ ያየሁት
ከዘራዬን ይዤ ሄድሁኝ ወጣሁት።

ሐሳብ ገብቶኝ እደጅ ሳሰላስል ቆሜ
ያን ቂዛዛ መስኮት ባስተውለው አግድሜ
አራዳ ግሪኮች እንደሚሸጡት
ያለ በያይነቱ አየሁኝ ብስኩት
ትዝ አለኝ «አራዳ አዲሳባ ሆይ

አገርም እንደ ሰው ይናፍቃል ሆይ ?» ...
አጎመዠኝ በሉ ሳይርበኝ ጠግቤ
አስተውለው ጀመረ መስኮቱን ቀርቤ።

የምገዛውንም በልቤ ቆጥሬ
ዳግም ልገባ ስል በስተበሩ ዞሬ
ዘወር ብዬ አያለሁ የውቴሉ ጌታ
ተኩሮ ያየኛል። ወደኔም ተጠጋ።
«ስንት ነው ሰውዬ ያንዱ ብስኩት ዋጋ ?»

የያዘው አባዜ ብሎት አላናግር
ዓይኑ ደም ለበሰ ይጉረጠረጥ ጀመር።
«ዓለም ሁሉ ያውቃል መሆኔን ታጋሽ ...
ትግሥቴ አሁን አልቋል።
ጥፋ ብረር ሽሽ !...
አገጭህን በቦክስ ሳላፈራርሰው
ይህ ፈጠጤ ዓይንህን እዚህ ሳላፈሰው
እሱቁ መግባትህ አንሶህ አሁንስ
መስኮቴ ፊር ደሞ ልትልከሰከስ ?!
ገበያ አላገኝም !
ደንበኞቼም
እዚህ አንተን ካዩ ደግመኛ አይመጡም።
ሥራ ሥራ እኮ ነው አይገባህም እንዴ ?
ወግድ ! አትገተር ይቋረጣል ንግዴ !»

ይህንን እንዳለ ቁጣው ጠና ጋለ።
አገጩና ጉንጩም በቡጢ ነገለ።

በቦክስም አይለኝም መልሶ መልሶ ..!
እስኪሸረፍ ድረስ ጥርሴ በደም ርሶ ..

ዝለጥ አደረግሁት በያዝኩት ከዘራ።
ገና አልጠቀመውም ዘበኛ ተጣራ።
ፖሊስ ቢሮ ሄድን።
እሱ ተለቀቀ።
አሸብር ከልካይ ግን እወህኒ ማቀቀ።

ማን ሊሰማኝ እዚያ ዘሬን ብቆጥር
ብሸልል ባቅራራ ወይስ ብፎክር ?
ደረቴ ላይ ያለው ያገሬ ባንዲራ
ያምራል ተባለ እንጂ ከብሮም አልተፈራ።

የሞጃው ተወላጅ የጠራሁት መንዜ
ሸጎሌ ሻንቅላ ተብዬ መያዜ

በግፍ እንደሆነ ባሰት በውሸት
አቃተኝ ማነንም ከቶ ማስረዳት።

ሲቸግረኝ ጊዜ አንዱን ተጠግቼ
«ሻንቆን» እንዲህ አልሁት ነገሬን አስልቼ፦
«ሰማኸኝ ወንድሜ አላሳዝንህም
በሰው ጠብ ገብቼ በከንቱ ስደክም ?

አውቃለሁ ከጥንትም ነጭና ሻንቅላ
በቁም እንደኖረ ሲዋጋ ሲጣላ።
እኔ ግን ሐበሻው ምን ወገን ልለይ ?
በማይነካኝ ነገር ለምን ልሰቃይ ?
እንካ ...ጠጉሬን እየው ...ሽጎሌ አይደለሁም።
ፊቴን ተመልከተው ..እንዳንተ አልጠቆርኩም።
ቀይ ዳማ ነኝ ..እየኝ ..ይሁን ጠይም ልባል፤ ..
እኔን መቁጠሪያ ራስ የሚለኝ ሰው አብዷል !
ዘራችንም ቢሆን ከነገደ ሴም
ሲወርድ የመጣ ነው ከዳዊት ካዳም።
የንግስተ ሳባን ታሪክ ሰምተህ የለ ?
ልጇ ቀዳማዊ ምኒልክ ተባለ ...
ዛጓማ ከገረድ ነው የተወለደ ...
አያወጣው ወጥቶ ከዙፋን ወረደ።

የካም ልጆች ናችሁ እናንተ ጥቁሮች
ፈረንጆችም ናቸው የያፌት ልጆች ...»
ብዬ እንደጀመርኩኝ ታሪክ ላስጠናው
ባጭሩ አቋረጠኝ ትእግስት አጣ ሰሚው።

«እንዲህ ያል ንግግር ያሰኛል አላቲ !
ባሻ አሸብር ከልካይ ልጠይቅህ እስቲ
ገና አንተ ነህና ኢትዮጵያዊ
አይደለሁም ልትል ጥቁር አፍሪካዊ ?!

ምን ይሆናል እንጂ አንተን ላይዘልቅህ
ነበረኝ ባያሌው ብዙ እምነግርህ ...

ቁጥርህ ከማን እንደሁ ከነጭ ወይ ጥቁር
ማወቅ ቢፈልግህ ወዳጄ አሸብር
እነጮች ቡና ቤት ገብተህ ቡና ጠጣ
ወይ በባቡር ስትሄድ አብረህ ተቀመጣ
ይህም ባይቻልህ ሞክር ባልደረባ
ነጮች እገቡበት ሆቴል ልትገባ።

ባንተ አልተጀመረም ያዳሜ ምኞት

ከተጠቃው «መራቅ» አጥቂን «መጠጋት»
ኃይለኛውን «መውደድ» ደካሙን «መጥላት» ...
ሰው ባያቱ ይምላል አባቱ ሳይከብር።
ማነው የድኃ ልጅ ዘሩን የማይቆጥር ?»

እስከ ዛሬ ድረስ ይህ አነጋገር
ሲታወሰኝ አለ ባሰብሁት ቁጥር።

ይመስገነው ገባኝ ከጊዜ በኋላ
አማራ፣ ...ራ፣ ...ና፣ ሻንቅላ
ሱማሌ፣ ኪኩዩ፣ ሡዋሂሊ፣ ባንቱ
ኩኑኑሉሉ፣ ማሣይ፣ ...ሮ፣ ባማንጓቱ
ማለት እንደሆነ ስልቻ ቀልቀሎ
ቀልቀሎ ስልቻ ስልቻ ቀልቀሎ
ስልቻ ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎ።

መንግስቱ ለማ